WITNESS STATEMENT OF TESFAHUN HAILU GEBREHIWOT

I, Tesfahun Hailu Gebrehiwot, born on PD of PD will say as follows;

1. I am the eldest brother of one of the victims of the November 2021 tragedy, Meron Hailu Gebrehiwet ("**Meron**").

2. I make this statement in order to provide relevant information to the ongoing Cranston Inquiry, based on my knowledge and understanding of the events under scrutiny. My statement should be read with the statement of my brother, Henok Hailu Gebrehiwot ('**Henok**').

3. The matters set out in this statement are within my knowledge unless otherwise stated. I wish to state that the events of 23/24 November 2021 were deeply traumatic for me, and I find it difficult to talk about losing my sister. The passage of three years has affected my ability to recall some details of the events leading up to and the events of 23/24 November 2021.

4. This statement was prepared with the assistance of my legal representatives at Duncan Lewis solicitors.

<u>Background</u>

5. I was raised by my parents in Adigrat, Tigray. I left the family home to study Accountancy at Mekelle University in 2002. After graduating, I moved to Addis Ababa to find work. Between November 2020 and November 2022, Ethiopia experienced a civil war, called the Tigray War. This was an armed conflict between the Ethiopian Government, with assistance from Eritrea, and the Tigray People's Liberation Front ('**TPLF**'). As a result of this conflict, many Tigrayans were displaced and there was widespread destruction of homes, property and land and disruption to our lives. Nowhere in Tigray was safe. During the conflict, I worked as a construction labourer to support the family. I own a car rental business PD I have a wife and three sons.

6. Meron was born in Adigrat, Tigray. Our father is Hailu Gebrehiwot and our mother is Libanos Berhe. Together they had seven children: Tsigereda (female), me (male), Birtukan (female), Ashenafi (male), Desbele (male), Henok (male) and Meron. Our father also has another child, Birhane. I do not recall everyone's dates of birth. We all lived in Adigrat as

a family when we were growing up. Meron was the youngest and was the centre of our family bond. She was the one who always brought us all together. Before the conflict, she was living a happy life. She was a beautiful woman. She was very small and slim. Meron did not have any medical conditions that I was aware of. Meron was not married or engaged. I think she believed in making a good life for herself and providing for her parents first, before settling down.

Ethiopia

7. Meron came to Addis Ababa for the first time in 2014. She studied computer science at Addis Ababa University, but she left university in her third year without graduating because she was more interested in being a business owner than studying. When she left university, she opened a takeaway food business. The business operated from 2017-2019 but eventually Meron had to close the business because it was not making enough money.

8. After her business closed in 2019, Meron moved back to Adigrat to be with our parents. Meron and my other sister Birtukan decided to go into business together. They opened a juice bar serving fresh fruit juice and milkshakes. They were quite successful and were making a good profit.

9. Meron and Birtukan continued to run their juice business until the war broke out in November 2020. During the Tigray War, the Ethiopian government began a military attack in Tigray. They were assisted by the Eritrean Defence Forces (‘**EDF**’). The Ethiopian and Eritrean Forces together formed an alliance (‘**the Allied Forces**’). During the war, a lot of civilian areas including hospitals, schools and other buildings were destroyed. Adrigat is in Tigray, and is very close to the Eritrean border. Due to the proximity of Adigrat to Eritrea, when the conflict broke out and the EDF joined the conflict, our town was quickly brought under the control of the EDF.

10. At the time that the war broke out, all of my family except my brother Henok were still in Tigray. Henok was in Addis Ababa. I was living in Adigrat with the rest of our family. As a family we felt that we needed to flee Adrigat as it was not safe. In mid-November 2020, I left Adrigat with my wife and son, my mother, Meron, my sister Birtukan and her eight-year-old and four-year-old sons.

11. My father stayed in Adigrat as he believed he would slow us down. He wanted to die in his home. At the beginning we travelled together in my car. After a while, I abandoned my car in Wukro, a town in Tigray around 85km south of Adrigat, because we had to find a more remote area to stay. I cannot remember exactly when this was. It was too dangerous to travel by car in these areas as the terrain was too rocky and mountainous. We had to walk from place to place after that, trying to escape the conflict and find a safe place to

stay. We travelled around to lots of different towns and villages in Tigray, such as Wukro, sometimes returning to places we had been; we could not stay anywhere too long.

12. It was a horrific life, it was a warzone. I felt a lot of responsibility as the man to care for my family. I think that Meron was deeply affected and traumatised by this period of our lives. The war and the displacement were extremely difficult for her. Meron was having nightmares about what she was seeing when awake: we saw total destruction of buildings, homes and lives completely destroyed. The whole region was a battlefield with constant gunfire, overturned cars, crying and bullets. I could not soothe her. Meron tried to be strong and although she never explicitly said to me that her mental wellbeing was suffering, I could see that the situation had taken a huge toll on her.

13. We survived by going door to door to beg for food. Meron often went to the doors of the rural houses to ask for help. She was able to support the family that way. But eventually bombs started being dropped in the rural areas. The people who lived in rural areas blamed those of us who had come from the cities for bringing the bombs to them. It was a superstitious belief. After that, they would not help us. Meron was even held captive by one farmer who blamed her for bringing the war to them and we had to beg for her life. When we went to request her release, they held us captive as well. We only escaped as there was heavy artillery being fired in the area, which caused a distraction as everyone was running for cover.

14. After nearly two months of moving around, in early January 2021, our family had no choice but to split up. My mother and siblings decided they would return to our home in Adigrat. They decided as a family that if they were going to die, they wanted to die at home with my father. Unfortunately my son, who was only one year old at the time, was sick and my wife and I decided we could not take our chances travelling with him until his health improved. We therefore had to stay back in Wukro for a day until he recovered. My mother and siblings, including Meron, walked around 85 kilometres back to Adigrat from Wukro. This took them around two days. They stayed overnight in Edga Hamus, which is around 30km from Adrigat. After approximately one day my son had recovered enough so that we could join them. We also returned to Adigrat on foot, walking for two days. My family spent a night in Negash, which is not far from Wukro.

15. By early 2021, the Allied Forces controlled most of Tigray and begun to reopen roads previously closed due to the conflict. In January 2021, once the roads had opened, I went to Addis Ababa to escape the war and the armed groups forcing people to fight. I had lived there between 2005 and 2012. My wife and son stayed in Adigrat. It would not have been safe for them to make the journey. In order to cross the internal borders inside Ethiopia, I had to pretend I was from Addis Ababa using my ID card issued from the capital. Tigrayans were not allowed to leave so it was the only way.

16. The environment in Addis Ababa was very hostile for Tigrayans at that time. There were random military checkpoints set up where people would be asked to show their ID; for Tigrayans this marked us out as a target for abuse. We could not find work and Tigrayans would be randomly detained by the police. I stayed in Addis Ababa for about one month with my cousin Zeresnay.

17. After about one month, I decided to leave Addis Adaba and make my way to South Sudan to find work. I did this so I could earn money to provide for my family, who had stayed in Adrigat. I had previously worked in Juba from 2012 -2019 (after I left Addis Ababa). I flew on a working visa from Addis Ababa to Juba.

18. Two weeks after I left Ethiopia, Meron travelled from Tigray to Addis Ababa. This was in mid-February 2021. She called me to tell me that she had left. She warned me that I needed to get my wife out of Tigray as soon as possible as the Federal forces were carrying out mass rapes against the Tigrayan women. She was very frantic and worried about my wife. She didn't say more than this, I think it was too painful to talk to me about it.

19. Between February and October 2021, Meron lived in Addis Ababa in our auntie's house with our female cousins. She spent her time there in hiding and trying to find a route out of Ethiopia. She was not able to work, and she did not feel safe leaving the house being a Tigrayan woman. When our cousin was detained, she understood the danger to her life if she remained. I recall that most of my conversations with Meron around that time were about her friends who had already fled to Europe because of the conflict. She would tell me again and again that she needed to find some way to get somewhere safe. I had been sending money to Ethiopia from South Sudan and helping her as much as I could. I think Meron also borrowed money from money lenders. She told me she was using the money to try to find routes out of Ethiopia. I do not know any of the arrangements as to how she left Ethiopia and I do not know if she used an agent to help her.

<u>Journey from Ethiopia to France</u>

20. Meron left Ethiopia in October 2021. Our family, who were still in Tigray at this point, did not know that Meron had left Ethiopia. Meron had been in Addis Ababa and although she did have a phone, due to the conflict in Tigray communication was cut off. This meant it was hard to get messages to our family. I was better able to communicate with her as I was in South Sudan, but we still did not communicate as much as I would have liked because of the difficult situations we were both in at that time.

21. Meron travelled from Ethiopia to Hungary by plane. I think she felt this was the safest option as leaving by foot to a neighbouring country was dangerous. I think she may have

been assisted by someone who helped her to get a visa, and Hungary was the easiest country to secure a visa from. Although, securing the visa to Hungary was still very difficult and cost a lot of money. I had been aware of her plans to fly to Hungary, but do not know if she intended to go to the UK from the outset, or if circumstances changed and she had no other option but to try and reach England.

22. I spoke to Meron about twice a week on the phone after she left Tigray until around a week before she passed away. All the time, she was telling me she was safe in Europe. She was travelling by trains through Europe with her friend Niyat Tewelde, who was also a victim of the tragedy on 23/24 November. As far as I know it was just the two of them travelling together. I do not know how they met each other or if they left Ethiopia together.

23. I sent Meron money once whilst she was in Europe; it was about a week after she left Ethiopia. I sent the money through a money transfer where I gave the money to someone in South Sudan who arranged to get the money to her through connections they had. I cannot remember exactly where Meron was at the time, I think she was still in Hungary.

24. The last time I heard from her I think she was in Belgium. This was around mid-November 2021. I did not know that she went to France or had any plans to go to the UK. I was not aware that she had attempted to travel to the UK by lorry or that she was going to attempt to cross the channel by boat.

Aftermath to the incident

25. I was in South Sudan when I learned that Meron had passed away, a few weeks after the incident. My friends in Juba became aware of the tragedy and took my phone away from me so I did not read it online; they were trying to protect me. I do not know how they found out that she was one of the victims, but I think that there were posts on social media which included her name as one of the people who died. My friends sat me down and told me. I could not believe it. I cannot put the grief into words.

26. My friends told me that Henok had been told a few days prior by our uncle, Hailu Berthe, who lives in Addis Ababa. Henok has since told me that he was invited around to my uncle's house and told early in the morning, as is the custom in Ethiopia. I could not control my grief and avoided speaking to my family for a few weeks after that. I understand that our parents learned about the tragedy and Meron's death a couple of weeks after my brother Henok found out.

Burial

27. Due to the conflict in Tigray, Meron had to be buried in Lille in France. There were restrictions on travel to and from the Tigray region, especially from Europe which meant they could not safely repatriate her body home. I think it was also too expensive. This is a great source of pain for our family, especially my mother. To this day, my understanding from Henok is that one of our cousins identified the body and to-date she the only member of our family who has seen the grave in France. It is our wish that her body is returned to Ethiopia.

Impact

28. Everyone is feeling grief and sadness, and the family cannot cope with the loss. We cannot bear to spend time together as a family anymore because we feel Meron's absence. We cannot be together without thinking of her, and what we lost. It is a misery every day.

29. Our mother cries every day thinking of Meron. Recently we went to our family home and removed some pictures of Meron, because our mother cannot cope with seeing them every day. Even though it has been nearly three years it still feels like a fresh wound for our family.

30. This has been a heart-breaking experience, and we hope to find closure once and for all. That is our ultimate desire, but every time we have to think about what happened to her it rips the pain open again. We want her to be remembered and respected. We need to be able to process the pain we are feeling so we can continue living our lives. We hope that the Inquiry can give us the answers and closure we need to be able to continue our lives without her.

Statement of Truth

I believe the facts stated in this witness statement are true. I understand that proceedings for contempt of court may be brought against anyone who makes, or causes to made, false statement in a document verified by a statement of truth without an honest belief in its truth.

Signed:

Date:

Name:

Docusign Envelope ID: E12A304E-007B-4F3B-ADAC-492E8312CA35

Habibi Interpreting and Translation LTD
35 Pinner Park Avenue, Harrow, London, HA2 6JY
Email: info@habibi-interpreting.co.uk
Contact: PD 181 / PD 933

የተስፋሁን ኃይሉ ገብረህይወት ምስክርነት ቃል

1. ተስፋሁን ኃይሉ ገብረሕይወ Personal Data የተወለደው Personal Data እንዲህ ይላል።

1 በህዳር 2014 በደረሰው አደጋ ሰለባ ከሆኑት አንዷ ሜሮን ሃይሉ ገብረህይወት ("ሜሮን")ታላቅ ወንድም ነኝ።

2 ይህንን ቃል የሰጠሁት በምርመራ ላይ ስላሉት ክስተቶች ባለኝ እውቀት እና ግንዛቤ ላይ በመመስረት በመካሄድ ላይ ላለው የCranston Inquiry ጠቃሚ መረጃ ለመስጠት ነው። የነ ቃል ከወንድሜ ሄኖክ ኃይሉ ገብረህይወት ('ሄኖክ') ቃል ጋር ይነበብ።

3 በዚህ የምስክርነት ቃል ላይ የተቀመጡት ጉዳዮች በሌላ መልኩ ካልተገለጸ በቀር እኔ የማቃቸው ጉዳዮች ናቸው። በኅዳር 14/15, 2014 የተከሰቱት ክስተቶች ለእኔ በጣም አሰቃቂ እንደነበሩ ለመግለፅ እወዳለሁ፤ እና እህቴን ስለማጣት ማውራት ይከብደኛል። ሶስት አመታት ስላለፉ እስከ ኅዳር 14/15, 2014 ድረስ የሆኑትን ነገሮች እና በእለቱ የተከናወኑትን አንዳንድ ዝርዝሮችን ለማስታወስ ይከብደኛል።

4 ይህ ቃል የተዘጋጀው በዱንካን ሉዊስ የሕግ አማካሪዎች የሕግ ወኪሎቼ እርዳታ ነው።

የኋላ ታሪክ

5 ወላጆቼ ያሳደጉኝ አዲግራት ትግራይ ላይ ነው። በ1994ዓ.ም. ቤተሰቤን ትቼ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ አካውንቲንግ ለመማር ሄድኩኝ። ከተመረቅኩ በኋላ ሥራ ለማግኘት ወደ አዲስ አበባ ሄድኩ። ከህዳር 2013 እስከ ህዳር 2015 ባለው ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ የትግራይ ጦርነት የሚባል የእርስ በርስ ጦርነት አጋጥሟት ነበር። ይህ በኢትዮጵያ መንግስት ከኤርትራ እርዳታ ጋር እና በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) መካከል የተደረገ የታጠቂዎች ግጭት ነበር። በዚህ ግጭት ብዙ የትግራይ ተወላጆች ተፈናቅለዋል፤ ቤት፣ ንብረትና መሬት ወድሟል እንዲሁም በሕይወታችን ላይ ረብሻ ፈጥሯል። ትግራይ ውስጥ የትኛውም ቦታ ደህና አልነበረም። በግጭቱ ወቅት ቤተሰቤን ለመደገፍ በግንባታ ሠራተኛነት ሠርቻለሁ Personal Data የመኪና ኪራይ ድርጅት አለኝ። ሚስት እና ሶስት ወንዶች ልጆች አሉኝ።

6 ሜሮን የተወለደችው አዲግራት ትግራይ ነው። አባታችን ሀይሉ ገብረህይወት እና እናታችን ሊባኖስ በርሄ ይባላሉ። እነሱ አንድ ላይ ሰባት ልጆችን ወለዱ: - ጽጌረዳ (ሴት) ፣ እኔ (ወንድ) ፣ ብርቱካን (ሴት) ፣ አሸናፊ (ወንድ) ፣ ደስበለ (ወንድ) ፣ ሄኖክ (ወንድ) እና ሜሮን። አባታችን ብርሃኔ የሚባል ሌላ ልጅም አለው። የሁሉንም ሰው የልደት ቀን አላስታውስም። ልጅ እያለን ሁላችንም አዲግራት ውስጥ እንደ አንድ ቤተሰብ ነበር የኖርነው። ሜሮን የሁላችሀንም ታናሽ የነበረች እና ቤተሰባችን በአንድ የምታስተሳስረው እሷ ነበረች። ሁላችንንም የምታሰባስብ እሷ ነበረች። ከግጭቱ በፊት ደስተኛ ህይወት ትኖር ነበር። ቆንጆ ሴት ነበረች። እሷ በጣም ትንሽ እና ቀጭን ነበረች። ሜሮን እኔ የማውቀው ምንም አይነት የጤና እክል አልነበራትም። ሜሮን አላገባችም ወይም አልታጨችም ነበር። እሷ ከማግባቷ በፊት ለራሷ ጥሩ ሕይወት መመስረት እና በቅድሚያ ወላጆቿን በመርዳት ታምን የነበረ ይመስለኛል።

ኢትዮጵያ

7 ሜሮን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ የመጣችው በ2007 ነው ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኮምፒውተር ሳይንስ ተምራለች ነገርግን ከመማር ይልቅ የንግድ ሥራ ባለቤት የመሆን ፍላጎት ስለነበራት ሳትመረቅ በሶስተኛ አመቷ ዩኒቨርስቲውን ለቃለች። ከዩንቨርስቲ ከለቀቀች በኋላ የተዘጋጀ ምግብ ቤት ለቤት የማቅረብ ስራ ንግድ ከፈተች። ንግዱ ከ2009-2011 የሰራ ቢሆንም በመጨረሻ ግን ሜሮን በቂ ገንዘብ ባለማግኘቷ ስራውን መዝጋት ነበረባት።

8 በ2011 ንግዷ ከተዘጋ በኋላ ሜሮን ከወላጆቻችን ጋር ለመሆን ወደ አዲግራት ተመለሰች። ሜሮን እና ሌላኛዋ እህቴ ብርቱካን አብረው ወደ ንግድ ስራ ለመግባት ወሰኑ። ትኩስ የፍራፍሬ ጭማቂ እና የወተት ጭማቂዎችን የሚያቀርብ የጭማቂ ባር ከፈቱ። በዛም በጣም ስኬታማ ነበሩ እና ጥሩ ትርፍም እያገኙ ነበር።

9 ሜሮን እና ብርቱካን ጦርነቱ በኅዳር 2013 እስኪከፈት ድረስ የጭማቂ ንግዳቸውን ቀጥለው ነበር። በትግራይ ጦርነት ወቅት የኢትዮጵያ መንግስት በትግራይ ላይ ወታደራዊ ጥቃት ጀመረ። በኤርትራ መከላከያ ሰራዊት ('ኢ.ዲ.ኤፍ')ም እየታገዙ ነበር። የኢትዮጵያ እና የኤርትራ ጦር በአንድነት ህብረት ፈጠሩ ('የተባበሩት ኃይሎች')። በጦርነቱ ወቅት ሆስፒታሎች፣ ትምህርት ቤቶች

Docusign Envelope ID: E12A304E-007B-4F3B-ADAC-492E8312CA35

Habibi Interpreting and Translation LTD
35 Pinner Park Avenue, Harrow, London, HA2 6JY
Email: info@habibi-interpreting.co.uk
Contact: PD 181 / PD 933

እና ሌሎች ሕንፃዎችን ጨምሮ ብዙ ሲቪል አካባቢዎች ወድመዋል። አድግራት ትግራይ ውስጥ ነው፣ እና ለኤርትራ ድንበር በጣም ቅርብ ነው። አዲግራት ለኤርትራ ባለው ቅርበት ምክንያት ግጭቱ ሲቀሰቀስ እና የኤርትራ መከላከያ ሰራዊት ወደ ግጭት ሲገባ ከተማችን በፍጥነት በኤርትራ መከላከያ ሰራዊት ቁጥጥር ስር ወደቀ።

10 ጦርነቱ በተቀሰቀሰበት ወቅት ከወንድሜ ሄኖክ በስተቀር ሁሉም ቤተሰቦቼ ትግራይ ውስጥ ነበሩ። ሄኖክ አዲስ አበባ ነበር። እኔ ከሌሎቹ ቤተሰቦቻችን ጋር አዲግራት ውስጥ ነበር የምኖረው። አዲግራት ሰላም ስላልነበር እንደ ቤተሰብ ከአድሪጋት መሸሽ እንደሚያስፈልገን ተስማማን። ኅዳር 2013 አጋማሽ ላይ፣ ከባለቤቴ እና ከልጄ፣ ከእናቴ ፣ ከሜሮን፣ ከእህቴ ብርቱካን እና ከስምንት አመት እና ከአራት አመት ወንድ ልጆቿ ጋር ከአዲግራት ወጣን።

11 ያዘገየናል ብሎ ስላመነ አባቴ እዛው አዲግራት ቀረ። በቤቱ ውስጥ መሞት ፈልጎ ነበር። መጀመሪያ ላይ በኔ መኪና ውስጥ ነበር አብረን የተጓዝነው። ከትንሽ ቆይታ በኋላ ከአዲግራት በስተደቡብ 85 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው የትግራይ ከተማ ውቅሮ ውስጥ መኪናዬን ተውኩት፣ ምክንያቱም እዛ ለመቆየት የበለጠ ራቅ ያለ እና የማይመች ቦታ መፈለግ ነበረብን። ይህ መቼ እንደነበረ በትክክል ማስታወስ አልችልም። መሬቱ በጣም ድንጋያማ እና ተራራማ በመሆኑ በእነዚህ አካባቢዎች በመኪና መጓዝ በጣም አደገኛ ነበር። ከግጭቱ ለማምለጥ እና አስተማማኝ ማረፊያ ለማግኘት እየሞከርን ከዚያ በኋላ ከቦታ ወደ ቦታ መጓዝ ነበረብን። እንደ ውቅሮ ባሉ ብዙ የትግራይ ከተሞችና መንደሮች ተዘዋውረን አንዳንዴ ወደ ነበርንበት ቦታ እንመለሳለን። የትም ቦታ ለረጅም ጊዜ መቆየት አልቻልንም ነበር።

12 በጣም አሰቃቂ ህይወት ነበር ፤ የጦር ቀጠና ነበር። ወንድ እንደመሆኔ ቤተሰቤን የመንከባከብ ትልቅ ኃላፊነት ተሰምቶኝ ነበር። በዚህ የህይወታችን ወቅት ሜሮን በጣም የተጎዳች እና የተሰቃየች ይመስለኛል። ጦርነቱ እና መፈናቀሉ ለእሷ እጅግ ከባድ ነበር። ሜሮን በቀን ሳትተኛ እያየችው ያለውን ነገር ስትተኛ ያቃዣት ነበር ፤ ህንፃዎች ሙሉ በሙሉ ሲወድሙ፣ ቤቶች ሲፈርሱ እና ህይወት ሲጠፋ እናይ ነበር። ክልሉ የማያቋርጥ ተኩስ የተከፈተበት ፣ የተገለበጠ መኪና፣ ለቅሶ እና ጥይት ያለበት የጦር አውድማ ነበር። እሷን ማረጋጋት አልቻልኩም። ሜሮን ጠንካራ ለመሆን እየሞከረች እና ምንም እንኳን የአእምሮ ጤንነቷ እየተሰቃየ እንደሆነ በግልፅ ነግረውኝ የማያውቅ ቢሆንም፣ ሁኔታው በእሷ ላይ ትልቅ ጉዳት እንዳደረሰባት ለማየት ችያለሁ።

13 ምግብ ከቤት ወደ ቤት እየሄድን እየለመን ነበር የቆየነው። ሜሮን ብዙ ጊዜ እርዳታ ለማግኘት ወደ ገጠር ቤቶች ደጃፍ ትሄድ ነበር። ቤተሰባችንን በዚህ መንገድ መደገፍ ችላለች። በመጨረሻ ግን በገጠር አካባቢዎች ቦምቦች መጣል ጀመሩ። በዚህም በገጠር አካባቢ የሚኖሩት ሰዎች እኛን ከከተማ የመጣነውን ሰዎች ቦምቡን ወደኛ አመጣችሁ ብለው ተጠያቂ አደረጉን። ያ አጉል እምነት ነበር። ከዚያ በኋላ እኛን መርዳት አቆሙ። ሜሮን ጦርነቱን ወደ እነርሱ አምጥታለች ብሎ በወነጀላት በአንድ ገበሬ ታግታ ህይወቷን ለማትረፍ መለመን ነበረብን። እሷን እንዲለቋት ልንጠይቅ ስንሄድ እኛንም አስረውን ነበር። በአካባቢው ከባድ መሳሪያ እየተተኮሰ ስለነበር ሁሉም ሰው ለመሸሽግ ሲሮጥ ግርግር ሲፈጠር ነበር እኛ ያመለጠነው።

14 ለሁለት ወራት ያህል ከተዘዋወርን በኋላ፣ በጥር 2013 መጀመሪያ ላይ፣ ቤተሰባችን ከመለያየት በስተቀር ሌላ ምርጫ አልነበረውም። እናቴ እና እህቶቼ ወደ አዲግራት ቤታችን ለመመለስ ወሰኑ። የሚሞቱ ከሆነ እነሱም እንደቤተሰብ ከአባቴ ጋር አንድላይ እቤት ውስጥ መሞት ፈለጉ። እንደ አለመታደል ሆኖ በወቅቱ የአንድ አመት ህጻን የነበረው ልጄ ታሞ ነበር እና እኔና ባለቤቴ ጤንነቱ እስኪሻሻል ድረስ እሱን ይዘን መጓዝ እንደማንችል ወሰንን። ስለዚህም እሱ እስኪያገግም ድረስ ለአንድ ቀን ውቅሮ መቆየት ነበረብን። እናቴ እና እህቶቼ ሜሮን ጨምሮ ከውቅሮ 85 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደምትገኘው ወደ አዲግራት በእግራቸው ተጓዙ። ይህም ሁለት ቀን አካባቢ ወስዶባቸዋል። ከአዲግራት 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው በእድጋ ሀሙስ አድረው ነበር። በግምት ከአንድ ቀን በኋላ ልጄ ከእነሱ ጋር እንድንቀላቀል በበቂ በሆነ ሁኔታ አገግሞ እኛም ለሁለት ቀናት በእግራችንም ተጉዘን ወደ አዲግራት ተመለስን። የኔ ቤተሰብ ከውቅሮ ብዙም በማይርቀው ነጋሽ አደርን።

15 በ2013 መጀመሪያ ላይ የተባበሩት ኃይሎች አብዛኛውን የትግራይ ክፍል ተቆጣጥረው በግጭቱ ምክንያት ቀደም ሲል የተዘጉ መንገዶችን መክፈት ጀመሩ። በጥር 2013፣ መንገዶቹ ከተከፈቱ በኋላ፣ ታጣቂዎቹ ህዝቡን እንዲዋጋ እያስገደዱ ስለነበር እና ከጦርነቱ ለማምለጥ ወደ አዲስ አበባ ሄድኩ።። ከ1997 እስከ 2004 እዛ ነበር የኖርኩት። ባለቤቴና ልጄ አዲግራት ቀሩ። ከኔ ጋር ቢጓዙ ኖሮ ለእነርሱ አስተማማኝ ባልሆነ ነበር። የኢትዮጵያን የውስጥ ወሰን ለመሻገር ከዋና ከተማው የተሰጠ መታወቂያዬን ተጠቅሜ የአዲስ አበባ ሰው እንደሆንኩ ማስመሰል ነበረብኝ። የትግራይ ተወላጆች እንዲወጡ አልተፈቀደላቸውም ነበር ስለዚህ ብቸኛው መንገድ ይሄ ነበር።

16 በአዲስ አበባ የነበረው ሁኔታ በወቅቱ ለትግራይ ተወላጆች ከፍተኛ ጥላቻ ነበረው። ሰዎች መታወቂያቸውን እንዲያሳዩ የሚጠየቁበት የዘፈቀደ ወታደራዊ ኬላዎች ነበሩ፤ ለትግራይ ተወላጆች ይህ የጥቃት ኢላማ አድርጎናል። ስራ ማግኘት አልቻልንም እና የትግራይ ተወላጆች በዘፈቀደ በፖሊስ ይታሰሩ ነበር። እኔ አዲስ አበባ ከአጎቴ ልጅ ዘረሰናይ ጋር ለአንድ ወር ያህል ቆየሁ።

Habibi
Interpreting and Translation
Breaking the language Barrier

Habibi Interpreting and Translation LTD
35 Pinner Park Avenue, Harrow, London, HA2 6JY
Email: info@habibi-interpreting.co.uk
Contact PD 181 / PD 933

17 ከአንድ ወር ገደማ በኋላ አዲስ አበባን ለቅቄ ሥራ ፍለጋ ወደ ደቡብ ሱዳን ለመሄድ ወሰንኩ። ይህን ያደረግኩት በአዲግራት ያሉት ቤተሰቦቼን ለመርዳት ገንዘብ ለማግኘት ነው። ከዚህ ቀደም ከ2004 -2011 (ከአዲስ አበባ ከወጣሁ በኋላ) በጁባ ሠርቻለሁ። በስራ ቪዛ ከአዲስ አበባ ወደ ጁባ በረርኩ።

18 ከኢትዮጵያ ከወጣሁ ከሁለት ሳምንት በኋላ ሜሮን ከትግራይ ወደ አዲስ አበባ ተጓዘች። ይህ በየካቲት 2013 አጋማሽ ላይ ነበር። መሄዷን ልትነግረኝ ደውላልኝ ነበር። የፌደራል ሃይሎች በትግራይ ሴቶች ላይ የጅምላ መድፈር እየፈፀሙ ስለሆነ ባለቤቴን በፍጥነት ከትግራይ ማስወጣት እንዳለብኝ አስጠነቀቀችኝ። ስለ ሚስቴ በጣም ፈርታ እና ተጨንቃ ነበር። ከዚህ በላይ ምንም አላለቺኝም ፤ ስለዚ ነገር ማውራት በጣም የሚያም ይመስለኛል።

19 በየካቲት እና ጥቅምት 2014 በዚህ ጊዜ ሜሮን አዲስ አበባ ውስጥ በአክስታችን ቤት ከሴት የአክስታችን ልጆች ጋር ትኖር ነበር። እዚያ ተደብቃ ከኢትዮጵያ መውጫ መንገድ ለማግኘት ስትሞክር ጊዜዋን አሳልፋለች። ስራ መስራት አልቻለችም ነበር እና ትግራዋይ ሴት በመሆኗ ከቤት መውጣት አስፈርትዋት ነበር። የአክስታችን ልጅ ስትታሰር እዚያ ከቆየች በህይወቷ ላይ ያለውን አደጋ ተረድታ ነበር። በዛን ጊዜ ከሜሮን ጋር ያደረኩት አብዛኛው ንግግር በግጭቱ ሳቢያ ወደ አውሮፓ ስለተሰደዱ ጓደኞቿ እንደነበር አስታውሳለሁ። ደህና የሆነ ቦታ ለማግኘት የሚያስችል መንገድ መፈለግ እንዳለባት ደጋግማ ትነግረኝ ነበር። ከደቡብ ሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ገንዘብ ልኬ የምችለውን ያህል እየረዳኋት ነበር። ሜሮን ከገንዘብ አበዳሪዎችም ገንዘብ የተበደረች ይመስለኛል። ገንዘቡን ተጠቅማ ከኢትዮጵያ መውጫ መንገዶችን ለማግኘት እየጣረች እንደሆነ ነግራኝ ነበር። ከኢትዮጵያ እንዴት እንደወጣች ምን አይነት መንገድ እንደተጠቀመች አላውቅም እና እሷን የሚረዳት ወኪል ተጠቅማ እንደሆነም አላውቅም።

ከኢትዮጵያ ወደ ፈረንሳይ ጉዞ

20 ሜሮን በጥቅምት 2014 ከኢትዮጵያ ወጣች። በዚህ ጊዜ ትግራይ ውስጥ የነበሩት ቤተሰቦቻችን ሜሮን ከኢትዮጵያ እንደወጣች አላወቁም ነበር። ሜሮን አዲስ አበባ ነበረች ምንም እንኳን ስልክ ቢኖራትም በትግራይ ግጭት የተነሳ ግንኙነት ተቋርጦ ነበር። ይህ ማለት ለቤተሰባችን መልእክቶችን ማድረስ ከባድ ነበር። ደቡብ ሱዳን እያለሁ በተሻለ ሁኔታ ከእሷ ጋር መገናኘት ችያለሁ፣ ነገር ግን በዚያን ጊዜ ሁለታችንም በነበረን አስቸጋሪ ሁኔታ ምክንያት አሁንም የምፈልገውን ያህል አልተገናኘንም ነበር።

21 ሜሮን በአውሮፕላን ከኢትዮጵያ ወደ ሀንጋሪ ተጓዘች። ወደ ጎረቤት ሀገር በእግር መሄድ አደገኛ ስለሆነ ይህ በጣም አስተማማኝ አማራጭ እንደሆነ ተሰምቷታል ብዬ አስባለሁ። ምንም እንኳን ወደ ሃንጋሪ ለመሄድ የሚያስፈልገውን ቪዛ ማግኘት በጣም ከባድ እና ብዙ ገንዘብ የሚያስወጣ ቢሆንም፣ ቪዛ እንድታገኝ በሆነ ሰው ተረድታ ሊሆን ይችላል ብዬ አስባለሁ። ወደ ሃንጋሪ ለመብረር ያቀደችውን እቅድ አውቄ ነበር፣ ነገር ግን ገና ከጅምሩ ወደ እንግሊዝ ለመሄድ አስባ እንደሆነ፣ ወይም ሁኔታው እንደተቀየረ እና እንግሊዝ ለመድረስ ከመሞከር ውጪ ሌላ አማራጭ እንዳልነበራት አላውቅም ነበር።

22 ሜሮን ትግራይን ለቃ ከወጣች በኋላ ህይወትዋ ሊያልፍ አንድ ሳምንት አካባቢ እስኪቀረው ድረስ በሳምንት ሁለት ጊዜ ያህል በስልክ አናግራት ነበር። ሁል ጊዜ በአውሮፓ ደህና መሆኗን ትነግረኝ ነበር። በህዳር 14/15 የአደጋው ሰለባ ከሆነችው ከጓደኛዋ ኒያት ተወልደ ጋር በባቡር አውሮፓ ወስጥ እየተጓዘች ነበር። እኔ እስከማውቀው ድረስ አብረው የሚጓዙት ሁለቱ ብቻ ነበሩ። እንዴት እንደተገናኙ ወይም አብረው ከኢትዮጵያ ወጥተው እንደሆነ አላውቅም።

23 ሜሮን አውሮፓ እያለች አንድ ጊዜ ገንዘብ ልኬላታለሁ; ከኢትዮጵያ ከወጣች አንድ ሳምንት ገደማ ነበር። ገንዘቡን በገንዘብ ዝውውር ነበር የላኩት ፤ በደቡብ ሱዳን ለሚኖር ሰው ገንዘቡን ሰጥቼ እነሱ በነበራቸው ግንኙነት እንዲያደርሱላት አረኩ። ሜሮን በወቅቱ የት እንደነበረች በትክክል አላስታውስም፣ ሳስበው ሃንጋሪ ውስጥ የነበረች ይመስለኛል።

24 ከሷ ለመጨረሻ ጊዜ የሰማሁት ቤልጅየም እያለች ይመስለኛል። ይህ በኅዳር 2014አጋማሽ አካባቢ ነበር። ወደ ፈረንሳይ እንደሄደች ወይም ወደ እንግሊዝ የመሄድ እቅድ እንዳላት አላውቅም ነበር። ወደ ዩናይትድ ኪንግደም በጭነት መኪና ለመጓዝ እንደሞከረች ወይም መተላለፊያውን በጀልባ ለማቋረጥ እንደምትሞክር አላውቅም ነበር።

ከተፈጠረው ክስተት በኋላ

25 ደቡብ ሱዳን እያለሁ ፣ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ፣ ሜሮን ከዚህ አለም በሞት መለየቷን ሰማሁ። በጁባ ያሉ ጓደኞቼ ጉዳዩን ስላወቁ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ዜናውን እንዳላይ እኔን ለመጠበቅ አስበው ስልኬን ከእኔ ወሰዱብኝ። ከሟቾቹ መካከል አንዷ መሆኗን እንዴት እንዳወቁት ባላውቅም ከሟቾቹ መካከል አንዷ ሆና ስሟን ያካተቱ በማህበራዊ ድህረ ገጾች ላይ የተፃፉ ፅሁፎች የነበሩ ይመስለኛል። ጓደኞቼ እኔን አስቀምጠው ነገሩኝ። ማመን አቅቶኝ ነበር። ሀዘኑን በቃላት መግለጽ አልችልም።

Docusign Envelope ID: E12A304E-007B-4F3B-ADAC-492E8312CA35

Habibi
Interpreting and Translation
Breaking the language Barrier

Habibi Interpreting and Translation LTD
35 Pinner Park Avenue, Harrow, London, HA2 6JY
Email: info@habibi-interpreting.co.uk
Contact: PD 181 / PD 933

26 ጓደኞቼ ሔኖክ ከጥቂት ቀናት በፊት በአዲስ አበባ የሚኖረው አጎታችን ኃይሉ በርቴ እንዳረዳው ነግረውኛል። ሄኖክ ከዚያ በኋላ ወደ አጎቴ ቤት እንደተጠራ እና በማለዳ እንደተረዳ ነግሮኛል፣ ልክ እንደ ኢትዮጵያ ባህል። ሀዘኔን መቆጣጠር አልቻልኩም እና ከዚያ በኋላ ለተወሰኑ ሳምንታት ከቤተሰቤ ጋር ከመነጋገር ተቆጠብኩ። ወንድሜ ሄኖክ ካወቀ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ወላጆቻችን ስለ አሳዛኙ ሁኔታ እና ስለ ሜሮን ሞት እንዳወቁ ተረድቻለሁ።

<u>ቀብር</u>

27 በትግራይ ግጭት ምክንያት ሜሮን በፈረንሳይ ሊል መቀበር ነበረባት። በተለይም ከአውሮፓ ወደ ትግራይ ክልል የመሄድ እና የመመለስ እገዳዎች ተጥሎ ስለነበር ፣ይህ ማለት አስከሬኗን በሰላም ወደ ሀገር ቤት መመለስ አልተቻለም ። እኔም በጣም ውድ ነበር ብዬ አስባለሁ። ይህ ለቤተሰባችን በተለይም ለእናቴ ትልቅ የስቃይ ምንጭ ነው። እስከ ዛሬ ድረስ፣ ከሄኖክ የተረዳሁት ነገር አንዷ የአጎታችን ልጅ አስከሬኑን ለይታለች እና እስከ አሁን ድረስ በፈረንሳይ መቃብሯን ያየች የቤተሰባችን ብቸኛ አባል ነች። አስከሬኗ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ምኞታችን ነው።

<u>ተጽዕኖ</u>

28 ሁሉም ሰው ሀዘን እየተሰማው ነው ፣ እና ቤተሰቡ ይህን እጦት መቋቋም አልቻለም። የሜሮን አለመኖር ስለሚሰማን እንደ ቤተሰብ አብረን ጊዜ ለማሳለፍ አልቻልንም። እሷን እና ያጣነውን ነገር ሳናስብ አብረን መሆን አንችልም። በየቀኑ ስቃይ ነው።

29 እናታችን ሜሮንን እያሰበች በየቀኑ ታለቅሳለች። በቅርቡ ወደ ቤተሰባችን ቤት ሄደን አንዳንድ የሜሮን ፎቶዎችን አነሳን ፣ ምክንያቱም እናታችን በየቀኑ ያንን ማየት ስለማትችል። ምንም እንኳን ወደ ሶስት አመት የሚጠጋ ቢሆንም አሁንም ለቤተሰባችን እንደ አዲስ ቁስል ሆኖ ይሰማናል።

30 ይህ ልብ የሚሰብር ተሞክሮ ነው፣ እና ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፍትሄ እንደምናገኝ ተስፋ እናደርጋለን። ይህ የእኛ የመጨረሻ ፍላጎት ነው ፤ ነገር ግን በእሷ ላይ ስለደረሰው ነገር ማሰብ በሚኖርብን ጊዜ ሁሉ ህመሙን እንደገና ያገረሻል። እንድትታወስ እና እንድትከበር እንፈልጋለን። ህይወታችንን ለመቀጠል የተሰማንን ህመም በሂደት መልመድ መቻል አለብን። ጥያቄው ያለእሷ ህይወታችንን ለመቀጠል የሚያስፈልገንን መልስ እና መፍትሄ ሊሰጠን እንደሚችል ተስፋ እናደርጋለን።

<u>የእምነት ቃል</u>

በዚህ የምስክሮች ቃል ላይ የተገለጹት እውነታዎች እውነት ናቸው ብዬ አምናለሁ። በእውነት ላይ ሳይመሰረት የእምነት ቃል ላይ ውሸት በሚሰራ ወይም እንዲሰራ ባደረገ ማንኛውም ሰው ላይ የፍርድ ቤት ንቀት ክስ ሊቀርብ እንደሚችል ተረድቻለሁ።

ፊርማ Personal Data

ቀን 8/11/2024 | 14:28:55 GMT

ስም Tesfahun Hailu Gebrehiwot

I have translated the above text from English into Amharic language to the best of my knowledge, ability, and command of both these languages. *Translator:* Name *Date: 04/11/2024*